ቁጥር 5411

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

# ማ ሻ ሻ ል

## የተለመደ ሕግ ነው ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ።

### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ፪ኛ መጽሐፍ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴፬ኛው ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፯ ዓ ፣ ም ፣

ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ፓትረያርክ በሆኑ በ፯ኛው ዓመት ፤

ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

ያለ ደራሲው ፈቃድ ማሳተም
በሕግ የተከለከለ ነው ።

# መግቢያ ።

## እናሻሽል ።

## ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው

ይህ የሂሳብ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ምክንያት የኢትዮጵያ ልጆች ከአባቶቻቸው የወረሱትን ትምህርትና ባህል ሳይለቁ ዕውቀት ከአንዱም ከንዱ ማጥናትና ሁኔታውን አመዛዝኖ የተሻለውን ዓይነት መያዝ ተገቢ መሆኑን ለመግለጽ ነው ። በኢትዮጵያ ያልታወቀ ፤ ታውቆ ያልተጀመረ ሥራ ፈጽሞ አይገኝም ።

፩ኛ ከአፈር አንጥሮ ብረት ማውጣት ፤ ፪ኛ የሸማ ዕቃ አበጅቶ የአማረ ልብስ ሠርቶ መልበስ ፤ ፫ኛ ቀምበር አለዝቦ ገጥሞ በማስማማት ማረስ ፣ ፬ኛ በእናቶቻችን በኩል ልዩ ልዩ ዓይነት የሸክላ ዕቃዎች መሥራት ። ሌላም ይህን የመሳሰለ ብዙ ዕውቀት ከጥንት የቈየ መኖሩን የማያውቅ የለም ። ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መሠረታውያንን ዕውቀቶች መሥራት በጀመረችበት ጊዜ ምዕራባውያን ከዚህ የበለጠ ዕውቀት እንዳልነበራቸው የታወቀ ነው ፤ ነገር ግን በኢትዮጵያችን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ዕውቀቶች እንደ ሌሎቹ አገሮች አሻሽሎ ከፍ የሚያደርጋቸው ዕድለኛ ባለመነሣቱ ዕድል ፤ ዕድለኛውን ሲጠብቅ ቈይቶ በደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አርቆ ተመልካችነት ተሻሽሎ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዕውቀት አበባ አሸብርቃ ትታያለች ፤ ቤተ ክህነትም ያልነበራትን ክብር በደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ

www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ ።

ሥላሴ ዕድልና ፍጹም ተጋድሎ ክብሯን ተጐናጽፋ ኀያ ብፁዓን ጳጳሳት ለማግኘት ችላለች ። ይህ ሁሉ በማሻሻል የተገኘ ዕድገት ነው ።

፩ኛ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከጥንታውያን አባቶቻ ችን የተገኘውን ዕውቀት የበዓላትንና የአጽዋማትን አቈ ጣጠር እንዲሁም በዓመት የሚገኙ ቀኖችና በቀኖቹም ሁሉ የሆነውን የአየር ምርመራ አባቶቻችን ዕውቀታቸ ውን በማሻሻል አሳድገው የደረሱበትን ስንመለከት ሙሉ ደስታ ተጐናጽፈን ለሚጠይቀን ሁሉ የበቃ መልስ ለመ ስጠት እንችላለን ።

፪ኛ በሀገራችን ላይ የሚሰጠውን ትምህርት ፩ኛነትን ማግኘት የሚገባው የአገራችን ቋንቋ መሆን አለበት ። በሌላውም ሀገር የሀገሩን ቋንቋ የማያከብር የለም ። በእኛ ግን አሁን እንደምንሰማው በሕፃናቱ አንደበት የሚነገረው ሁሉ ፤ የቄስ ትምህርት የሚባል ስም ሰጥተውታል ። ይህ ሁኔታ በጣም ትልቅ ጥፋት ነው ። ሕፃናት በሕፃንነታቸው ወራት የነቀፉትን ኋላ በአደጉ ጊዜ ሊያከብሩት አይች ሉምና ፥ መምህራንና ወላጆች አስበውበት የሕፃናቱን አእምሮ እንዲሻሻል ማስተማርና መገሥፅ አለባቸው ። የሀገር ትምህርት ይባላል እንጂ የቄስ ትምህርት አይባ ልም ስል ሐሳቤን በትሕትና እገልጻለሁ ።

# ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው

## ፩ኛ መጽሐፍ

## የ፩ኛ ደረጃ ትምህርት

መጀመሪያ ማሻሻል ተገቢ መሆኑን ተገንዝበ በዓ ላትንና አጽዋማትን ተሻሽለው በተወሰኑላቸው ቀን እን ዲውሉ ያደረገ ቅዱስ ዲሜጥሮስ ነው በጊዜው የነበሩት ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንትም በመግባባት ተስማምተው ሐሣቡን አጽድቀውለት እስከ ዛሬ ድረስ ሲሠራበት ቆይቷል ።

የኢትዮጵያ ሊቃውንትም አሁን ባለንበት ዘመን የሕ ዝቡን ሁኔታ እየተመለከቱ በሕፃናቱ አእምሮ የሚቀ ረጹ ጥናቶች በማሻሻል ሃይማኖትን መሠረት አድርገው ማስተማርና ማስጠናት አለባቸው ።

አስረጅ ምሳሌ ም. ፳፪ ቁ. ፮ ልጅን በሚሄድ በት መንገድ ምራው በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይ ልም ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለዛሬው ትውልድ አባቶች የሆኑ ሁሉ የሥራ መምሪያ ሊሆናቸው ይችላል ።

## ፩ኛ ክፍል

አበቅቴ ማለት ተረፈ ዕለት (ቀን) ቍጥር ማለት ነው መጥቅዕ ማለት ነጋሪት ማለት ነው በቁሙም መጥቅዕ ማለት ነው ትርጓሜውም ሰብሳቢ ማለት ነው መጥቅዕ ከ፲፭ እስከ ፴ በመስከረም ከ፩ እስከ ፲፬ በጥቅምት ይውላል ከዕለታት ተውሳክ ጋር ተቆጥሮ ከ፴ ቢጐድል ወይም ፴ ቢሆን እንዳለ ከ፴ ቢተርፍ ፴ን ገድፎ ትር

www.ethiopianorthodox.org

ፉን ሐመር ይባላል ትርጓሜውም መሸጋገርያ ማለት ነው ።

የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀመራል የቅዳሜ ተውሳክ ፰ . . የእሁድ ተውሳክ ፯ የሰኞ ተውሳክ ፮ የማክሰኞ ፭ የረቡዕ ፬ የሐሙስ ፫ የዓርብ ፪ ነው በዘመነ ሐዲስ የተሠሩ የበዓላትንና የአጽዋማትን ተውሳክ በዓቢይ ጾም ይጀምራል የዓቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ የሆሣዕና ፪ (የፍሥሐ አሪት ፲) የስቅለት ፯ የትንሣኤ ፱ የረክበ ካህናት ፫ የዕርገት ፲፰ የጰራቅሊጦስ ፳፰ የጾመ ሐዋርያት ፳፱ የምህላ ድኅነት ፩ . . . ነው ።

ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ቍጥር በየአንዳንዱ ከመጥቅዕና ከተውሳከ ዕለት እየተጨመረ ሲቈጠር በዓመት በዓመቱ የሚገኘውን በዓላትና አጽዋማትን ያስገኛል የበዓላቱ ቀኖች (ነነዌ በዓተ ጾም ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ ፤ ደብረ ዘይት ሆሣዕና ትንሣኤ . . ጰራቅሊጦስ ከእሑድ ፤ ረክበ ካህናት ምህላ ድኅነት ከረቡዕ ፤ ዕርገት ከሐሙስ ፤ አይወጣም በዚህ ጸንቶ ይኖራል ።

ከዚህ ቀጥሎ ሠርቀ መዓልታቸውን ኢየዓርግና ኢይወርድ መመላለሻውን ይናገራሉ ። በዓለ መጥቅዕ የበዓላትንና የአጽዋማትን መሠረት ኢይወርዱ ፲፭ መጥቅዕ ተገኝቶ መስከረም ዓርብ ብቶ በዓለ መጥቅዕ መስከረም በ፲፭ኛው ቀን ዓርብ ቢውል አጽዋማት በዓላት በታሕታይ ቀመራቸው ይውላሉ ይኸውም ዓርብ እስከ ዓርብ ፰ ዓርብ እስከ ዓርብ ፲፭ የዓርብ ተውሳክ ፪ ፲፭ እና ፪ ፲፯ ይሆናል የኢይወርዱ መበጃ ሐመር ይኸ ነው ፤ የመጨ



ረሻው ታሕታይ ቀመራቸው ነነዌ ከጥር ፲፯ት አይወርድም ፤ ኢየዓርግ ፲፫ት መጥቅዕ ተገኝቶ መስከረም ቅዳሜ ብቶ ጥቅምት ሰኞ ብቶ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት በቢተ በ፲፫ ቀን ቅዳሜ ቢውል አጽዋማትና በዓላት በላዕላይ ቀመራቸው ይውላሉ ጥቅምት ሰኞ ይብታል ሰኞ እስከ ሰኞ ፰ ሰኞ እስከ ሰኞ ፲፭ እሁድና ሰኞ ሲቀነሱ ቅዳሜ ፲፫ት ይሆናል የቅዳሜ ተውሳክ ፰-፰ እና ፲፫ ፳፩ ይሆናል ላዕላይ ቀመራቸው ኢየዓርግ ነነዌ ቢወጣ ከየካቲት ፳፩ ወደ ፳፪ አይወጣም መመላለሻው ከጥር ፲፬ ቀን ከየካቲት ፳፩ ቀን ፴፭ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፪ኛ ዓቢይ ጾም ቢወርድ ከየካቲት ፩ ቀን ወደ ጥር ፴ ቀን አይወርድም ቢወጣም ከመጋቢት ፭ ቀን በላይ ወደ ፮ት አይወጣም መመላለሻው ከየካቲት ፴ ከመጋቢት ፭ ቀን ፴፭ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፫ኛ ደብረ ዘይት ከየካቲት ፳፰ ቀን በታች አይወርድም ቢወጣም ከሚያዝያ ፪ ቀን በላይ ወደ ፫ ቀን አይወጣም መመላለሻውም ከየካቲት ፫ ከመጋቢት ፴ ከሚያዝያ ፪ ቀን ፴፭ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፬ኛ ሆሣዕና ሲወርድ ከመጋቢት ፲፪ በታች አይወርድም ቢወጣም ከሚያዝያ ፳፫ ቀን አይወጣም መመላለሻው ከመጋቢት ፲፪ ከሚያዝያ ፳፫ ፴፭ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፭ኛ ስቅለት ሲወርድ ከመጋቢት ፳፬ በታች አይወርድም ቢወጣም ከሚያዝያ ፳፰ ቀን በላይ አይወጣም

www.ethiopianorthodox.org

መመላለሻው ከመጋቢት ፳፬ ቀን ከሚያዝያ ፳፰ ቀን ፴፭ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፮ኛ ትንሣኤ ሲወርድ ከመጋቢት ፳፮ በታች አይወርድም ቢወጣም ከሚያዝያ ፴ ቀን አይወጣም መመላለሻው ከመጋቢት ፳፮ ከሚያዝያ ፴ ፴፭ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፯ኛ ረክበ ካህናት ሲወርድ ከሚያዝያ ፳ ቀን በታች አይወርድም ቢወጣም ከግንቦት ፳፬ ቀን በላይ አይወጣም መመላለሻውም ከሚያዝያ ፳ ቀን ከግንቦት ፳፬ ቀን ፴፭ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፰ኛ ዕርገት ከግንቦት ፭ ቀን በታች አይወርድም ከሰኔ ፱ ቀን በላይ አይወጣም መመላለሻው ከግንቦት ፳፮ ከሰኔ ፱ ፳፮ና ፱ ፴፭ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፱ኛ ጰራቅሊጦስ ከግንቦት ፲፭ ቀን በታች አይወርድም ቢወጣም ከሰኔ ፲፱ ቀን በላይ አይወጣም መመላለሻው ከግንቦት ፲፭ ቀን ከሰኔ ፲፱ ቀን ፴፭ ይሆናል በዚሁ ሲመላለስ ይኖራል ።

፲ኛ ጾመ ሐዋርያት ሲወርድ ከግንቦት ፲፮ በታች አይወርድም ቢወጣም ከሰኔ ፳ ቀን በላይ አይወጣም መመላለሻው ከግንቦት ፲፮ ቀን ከሰኔ ፳ ቀን ፴፭ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፲፩ኛ ምህላ ድኅነት ከግንቦት ፲፰ ቀን በታች አይወርድም ቢወጣም ከሰኔ ፳፪ ቀን በላይ አይወጣም ከግንቦት ፲፰ ቀን ከሰኔ ፳፪ ቀን ፴፭ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል መመላለሻቸው ይህ ነው ።



## ፪ኛ ክ ፍ ል ።

ከዚህ ቀጥሎ ሥርዓተ ጥንተ ዮንን (ይናገራል) እና ስረዳለን ጥንተ ዮን ማለት ፀሐይ የተፈጠረበት ዕለተ ረቡዕ ነው ስለዚህ ጥንተ ዮን አንድ ብሎ የሚጀምር በት ቀን ረቡዕ መሆኑ ነውና አስተውል ጥንተ ዮንን ለማወቅ ስንፈልግ ዓመተ ዓለምን ከ፬ት ክፍለን መጠነ ራብዒትን ስድስተኛዪቱ ጳጉሜን ፭ኛ አክለን በ፯ በ፯ት ሱባኤ እንከፍለዋለን ከሱባኤ የተረፈውን አንዱን አትተን መስከረም የባተበትን ቀን እናገኛለን ።

አንድ ቢተርፍ የረቡዕ ጥንተ ዮን መሆኑ መስከረም ረቡዕ መባቱ በዚህ ይታወቃል ፤ ፪ት ቢተርፍ የሐሙስ ነው ፤ መስከረም ሐሙስ ይብታል ፤ ፫ት ቢተርፍ የዓርብ ነው መስከረም ዓርብ ይብታል ፤ ፬ት ቢተርፍ የቅዳሜ ነው መስከረም ቅዳሜ ይብታል ፤ ፭ት ቢተርፍ የእሁድ ነው መስከረም እሁድ ይብታል ፤ ፮ት ቢተርፍ የሰኞ ነው መስከረም ሰኞ ይብታል ፤ ፯ት ቢተርፍ የማክሰኞ ነው መስከረም ማክሰኞ ይብታል ፤ ጥንተ ዮን መነሻው ረቡዕ ነው መድረሻውም ማክሰኞ ነው ዕለተ ዮሐንስ ማለት የዘመን መለወጫ የሚውልበትን ወይም ያለፈውን ዘመን የዋለበትን ለማግኘት የሚያስችል ጥንተ ዮንን አስቀድሞ ማውጣት ነው እንደምን ቢሉ በዓመት በዓመቱ የደረስንበትን ዘመን መሠረት አድርገን ወደኋላ ያለውን ዘመን ከ፬ት ክፍለን መጠነ ራብዒት ፯ተኛዪቱን ጳጉሜን ጨምረን በሱባኤ በሱባዔ ብንከፍለው ከላይ እን

www.ethiopianorthodox.org

ዷተትነው የመቧቻውን ጥንተ ዮን ከሱባዔው ትርፍ ሆኖ እናገኘዋለን ያለፈውም የሚመጣውም በጠቅላላው በዚሁ ቍጥር ዕለታቱን ሁሉ ለማግኘት የሚያስችል ነውና እናስተውል ።

## ፫ኛ ክ ፍ ል ።

ሠርቀ ዕለት በእሁድ ይጀምራል ። በቅዳሜ ይጨርሳል ። በሠርቀ ዕለት ዕለተ ዮሐንስን ማለት የዘመን መለወጫ መስከረም የሚብትብትን ቀን ለማግኘት ስንፈልግ እንዳለፈው ዓመተ ዓለምን ከ፬ት ከፍለን መጠነ ራብዒት ፮ተኛዪቱን ጳጕሜን አክለን ጥንተ ዮኑን ካወጣን በኋላ የወጣውን ጥንተ ዮን አንዱን ሳናትት እንዳለ አቈይተን ፪ት ዕለተ ጠቢባን ጨምረን በሱባዔ ብንከፍል አሁንም ከሱባዔ የተረፈውን ሳናትት ፩ድ ቢተርፍ ዕለተ ዮሐንስ መስከረም ፩ ቀን እሁድ ይውላል ። ፪ት ቢተርፍ ሰኞ ፤ ፫ት ቢተርፍ ማክሰኞ፤ ፬ት ቢተርፍ ረቡዕ ፤፭ት ቢተርፍ ሐሙስ፤ ፮ት ቢተርፍ ዓርብ፤ ፯ት ቢተርፍ ቅዳሜ ይውላል ሠርቀ ዕለት ከሰባት አያልፍም ። እሁድ ዘወትር አንድ ዕለት ተብሎ ይቈጠራል ። አቈጣጠሩም እንደሚከተለው ነው ።

አሁን የ፲፱፻፶፮ ዓ ም. ጥንተ ዮንና ሠርቀ ዕለትን ማግኘት ዓመተ ዓለምን ለ፬ቱ ወንጌላውያን እናካፍለዋለን ።

ዘመኑም ፯ሺህ ፬፻፶፮ ዓመት ነው ለ፬ት ሲከፈል አንድ ሺህ ፰፻፷፬ ፩ሺህ ፰፻፷፬ ይደርሳል ወንጌላዊው ዮሐንስ



መሆኑ በዚህ ይታወቃል ስለበዓላቱም በ፩ኛው መጽሐፍ ከገጽ ፲፯ እንደገለጽነው ነው የ፩ዱን ክፍል በ፯ በ፯ ብንከፍለው ከ፩ሺህ ፰፻፷፬ ፪ ይተርፋል ከ፬ቱ ወንጌላውያን ፰ት ይተርፋል መጠነ ራብዒት ፮ተኛዪቱ ጳጕሜን ፩ሺህ ፰፻ ፷፬ ቀን ሆናለች፤ ይህም በ፯ በ፯ ሲከፍሉት ፪ት ይተርፋል ፪ት ዕለተ ጠቢባን ሲጨመር ፬ት ይሆናል ፰ና ፬ት ፲፪ት ይሆናል ።

፯ቱን ቢገድፉ ፭ ይቀራል ፩ዱን ሳያትቱ ይቈጠራል ስለዚህ ሐሙሱ ሠርቀ ዕለት ይባላል ። በ፶፮ ዓ. ም. ዕለተ ዮሐንስ መስከረም ፩ ቀን ሐሙስ መዋሉ በዚህ ይታወቃል ።

ሐሙስ በጥንተዮን ብቻ አቈጣጠር ፪ኛ ቀን ነው።
በሠርቀ ዕለት አቈጣጠር ፭ኛ ቀን ይሆናል ዕለተ ጠቢባን የተባሉትም እሑድና ሰኞ ናቸው ከቀመር ገብተው አልተቈጠሩምና ዕለተ ጠቢባን ተባሉ ።

የዕለታት መጀመሪያ እሑድ ነው ስሙም ጥንተ ዕለት ይባላል ፤ የቀመር የዓመታት ቍጥር መጀመሪያ ማክሰኞ ነው ስሙም ጥንተ ቀመር ይባላል የዓመታት ቍጥር መጀመሪያ ስለሆነ ነው ምክንያቱም ቅዱስ ድሜጥሮስ ፭ት ወር ከ፯ ቀን በኬክሮስ ገድሮ ሠሉሱ ማቴዎስ ብሎ ዓመታትን መቍጠር የጀመረበት ዕለት ስለሆነ ጥንተ ቀመር ይባላል ።

እሑድና ሰኞ ዕለተ ጠቢባን ተብለው የሠርቀ ዕለት ቍጥር ለማግኘት የሚያስችሉ መደበኞች ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥንተ ዮን ማለት ፀሐይና ጨረቃ ከዋክብት የተፈጠሩበት ዕለተ ረቡዕ ነው ። እሁድ ወሠሉስ ወረቡዕ ዘውእቶሙ ፫ቱ ጥንታት የሚአሰኘው ይህ ነው ።

## ፩ኛ ክፍል ።

አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን የሂሳብ ቍጥር ሲያስጠኑበት የኖረው ሁኔታ እንደሚከተለው ነው ። ከላይ በ፫ኛው ክፍል እንደገለጽነው የ፭ዱን ወንጌላዊ ክፍል በ፬ በ፬ት ሲከፍሉ ፪ት ይተርፋል ብለናል ።

በመጀመሪያ ፲ውን ዓመት በ፬ በ፬ ስንከፍለው ፫ ጊዜ ፬ት ፲፪ ይሆናል ። ከ፲ው ፫ ይቀራል ማለት ነው ።

፹፫ ጊዜ ፬ ፫፴፪ ይሆናል ከመቶው ፪ ይቀራል አስትውል ።

አሁን የ፭ዱን ክፍል ጠቅላላ ሂሳብ እናሳያለን ማለት የ፭ዱ ክፍል ፲፭፻፴፬ ዓመት ነው በዚሁ ውስጥ ስንት ጊዜ ፬ት እንዳለ እንወቅ ።

በዚሁ ውስጥ ፫፻፹፫ ጊዜ ፬ት ይገኛል በዚሁም ላይ ከ፬ ቀጥር የተረፈ ፪ት ይገኛል ።

ጥንተ ዮን ለማስገኘት ያስቻለ ይህ ፪ የተረፈ ቍጥር ነው (በ፪ኛው ክፍል ተመልከት ።)

አሁንም ጥንታዊው የአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን የአከፋፈል ሂሳብ በጥንታዊው አኃዝ ቍጥር እንዴት አድርገው ሲያስተምሩ ወይም ሲያስጠኑ እንደነበሩ ስንገልጽ አሰጣጡ የቃል ነው ሆኖም ከላይ እንደገለጽነው ፲፭፻፴ ፬ት ዘመን በ፬ በ፬ እንከፍለዋለን ።



## የ፭ዱ ወንጌላዊ ድርሻ ።

፫ ፻ ፹ ፫<br>
፲ ፭ ፻ ፴ ፬ ÷ ፬ት ጊዜ<br>
፲ ፪ ፻<br>
፫ ፻ ፴<br>
፫ ፻ ፳<br>
፲ ፬ —<br>
፲ ፪ —<br>
፪

፪ት ይተርፋል የተባለው ይህ ነው ።

ቀጥሎ ያለውን ተመልከት

፫፻ ጊዜ ፬ት ፲፪፻ ይሆናል ፹ ጊዜ ፬ ፫፻፳ ይሆናል ፫ት ጊዜ ፬ ፲፪ ይሆናል ።

ጥንታውያኑ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ያቆዩትን የሂሳብ ትምህርት የዛሬው ወጣት በእውቀት የደረጀ እንደመሆኑ መጠን ከአባቶቹ የወረሰውን እውቀት መሠረት አድርጎ ። የአዋቂዎች ልጅ መሆኑን ተገንዝቦ እውቀቱን ለወደፊት በበለጠ ሁኔታ ማስፋፋትና ማሻሻል አለበት እንጂ አይከለከልም ።

ኤውሮፓውያን እንደዛሬ ማይሆን በጥንታዊው ቍጥራቸው በጭረት ይቈጥሩ እንደነበሩና አሁንም የጥንቱ ቍጥራቸውን ያልሰረዙ መሆናቸውን የሚያስረዳ በየመጽሐፋቸው ጥንታዊውን አኃዝ ፩ ፩ ፩ ፫ት ሲሉ ፫ ጭረት ይጽፋሉ ። አሁን ግን በማሻሻል የቍጥራቸውን አኃዝ

www.ethiopianorthodox.org

የተጣራና ምቹ አድርገው ልጆቻቸውን እንደጠቀሙ ያስረዳል ። የተጣራ ሂሳብና አኃዝ መሠረቱ(ማለት የተገኘበት ሀገር) ከአፍሪቃ ክፍል ከዓረብ ሊቃውንት ነው ይባላል ።

ይህ ከላይ በጥንታዊው ቊጥር የተከፈለውን አከፋፈል በሐዲሱ የተሻሻለ ቊጥር ስናየው በሥራው ቀልጣፍ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን ይኸውም እንደሚከተለው ነው ።

የ፩ዓ ወንጌላዊ ክፍል 1864— ነው ።

```
  2 6 6
 1864 -7
 1  4
    4 6
     4 2
      4 4
       4 2 -2
```

266 ጊዜ 7 ይሆናል ሁለት ይተርፋል የተባለው ይህ ነው ።

ማንኛውንም ነገር ለማቃለል ተስማምቶ በማሻሻል የተሠራ እንደሆን ለመጭው ትውልድ የዕውቀት በር ከፋች ይሆንለታል ። እግዚአብሔርም በመስማማት የተሠራ ሁሉ እንደሚደሰትበት የታወቀ ነው ። ከላይ የጠቀስነው የምዕራባውያን ቊጥር ሦስት ጫረት ሦስት ብለው ይቈጥሩት



ነበር ። ዛሬ ግን በተሻሻለው አርምኛ የተከናወነው አቈጣጠር አንድ መቶ አሥራ አንድ ይሆናል ይህም በማሻሻል የተገኘ ነው ። በሀገራችንም ከአሁን በፊት ሊቃውንቱ እየተስማሙ መንቃቀፍን እያስወገዱ በመሥራታቸው ራሳቸውን ጠቅመው ልጆቻቸውን በደግነት ፥ በቅድስና ፥ በርኅራኄ ፥ መሥርተው አጽንተው ሄደዋል ። ከእኛ በፊት የነበሩ ልጆቻቸውም የእኛ አባቶች እንደመሆናቸው መጠን እንደ አባቶቻቸው በመስማማት የአባቶቻቸውን ሕግ በመጠበቅ እየሠሩ ብዙውን እያሻሻሉ ቈይተው ለእኛ አስረክበውን ሄደዋል ። እኛም ከአባቶቻችን ያገኘነውን ሥራና ደግነት መሠረት አድርገን ለመጭው ትውልድ ጊዜው በሚፈቅደው እየተከተልን የከበደውን ነገር በመስማማት እያሻሻልን ብንሠራ የልጆቻችን ዕውቀት ከማደጉም በላይ እኛም እንጠቀምበታለን እንኟ አንገሎዳበትም ልጆቻችንም ከሃይማኖታቸው አይርቁም ጥንታውያን አባቶቻቸውንም አይነቅፉም ። ልጅ አባቱን ሲነቅፍ ክብሩን ይቀንስበታል አባቱን ሲያከብር ግን የራሱንና የአባቱን ክብር ከፍ ያደርጋል ።

አስረጅ መጽሐፍ ቅዱስ፤ ምሳሌ ። ም ፲፯–ቊጥር ፮ት የሽማግሌዎች አክሊል የልጅ ልጆች ናቸው ። የልጆችም ትምክህት አባቶቻቸው ናቸው የሚለውን ስንመለከት በቁ መምሪያ ነው ምን ጊዜም የተውሶ አባት አባት ወይም ክብር አይሆንም ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ ክፍል ።

ተውሳከ ዕለት ከምን እንደተገኘ ከዚህ ቀጥለን እናስረዳለን ። የ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በ፩ኛው መጽሐፍ ገጽ ፲፯ ላይ እንደገለጽነው በዓለ መጥቅዕ የዋለበት ጥቅምት ፲፫ ቀን ሐሙስ ስለ ሆነ የሐሙስን ተውሳክ ለማግኘት የሚያስችለን መጥቅዕ የዋለበት ሳኒታ ማለት ከጥቅምት ፲፬ ቀን ጀምረን ነነዌ እስከ ዋለበት ቀን ስንቈጥር ፻፳፫ ቀን ይሆናል ። ፻፳ውን በ፴-በ፴-ቢገድፉ ፫ት ይተርፋል የሐሙስ ተውሳከ ዕለት የተባለ ይህ ነው ።

በዓለ መጥቅዕ ዓርብ ሲውል ፻፳፱ ዕለት ቅዳሜ ቢውል ፻፳፰ ። እሑድ ቢውል ፻፳፯ ። ሰኞ ቢውል ፻፳፮ ። ማክሰኞ ቢውል ፻፳፭ ። ረቡዕ ቢውል ፻፳፬ ቀን ይገኛል ። ከዚህ የሚወጣ ተውሳከ ዕለት የለም ። ሁልጊዜ ከመጥቅዕ ሳኒታ አንስቶ ነነዌ እስከ ዋለበት ቀን እየቈጠሩ ፻፳ውን በ፴-በ፴- እየገደፉ ተውሳከ ዕለት ይገኛል ። መጥቅዕ ከተውሳከ ዕለት ጋር ተቈጥሮ ጾመ ነነዌን ያስገኛል ።

የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ መሠረታቸው ነነዌ ነው ከነነዌ ሳኒታ እስከ በዓተ ጾም ፲፬ ቀን ይገኛል እስከ ደብረ ዘይት ፵፩ ቀን ይገኛል እስከ ሆሣዕና ፷፪ እስከ ስቅለት ፷፯ እስከ ትንሣኤ ፷፱ ቀን እስከ ረክበ ካህናት ፺፫ ቀን እስከ ዕርገት ፻፰ እስከ ጰራቅሊጦስ ፻፲፰ ቀን እስከ ጾመ ሐዋርያት ፻፲፱ ቀን እስከ ጾመ ድኅነት ፻፳፩ ቀን ይገኛል ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት በዓላት ተውሳካቸውን ለማግኘት (ተውሳክ ማለት ጭማሪ ማለት ነው ምክንያቱም በዓላቱን ለማግኘት ከመጥቅዕ ጋራ አብሮ እየተጨመረ የሚቈጠር ስለሆነ ነው) በየ አንዳንዱ ክፍል ያለውን ቍጥር ከ፴ በታች ያሉት እንዳሉ ሁነው ከ፴ በላይ ያሉትን ሁሉ በ፴ በ፴ እየገደፉ ትርፉን ከመጥቅዕ ጋራ እየጨመሩ ሲቆጥሩ በዓመት በዓመቱ የሚውሉበትን ቀን ለማግኘት እንችላለን ።



፩ኛ, የዓቢይ ጾም ፲፬| ፪ኛ የደብረ ዘይት ፲፩ ፫ኛ| የሆሣዕና ፪ ፬ኛ የስቅለት ፯ ፭ኛ| የትንሣኤ ፱ ፮ኛ| የረክበ ካህናት ፫ ፯ኛ| የዕርገት ፲፰ ፰ኛ| የጰራቅሊጦስ ፳፰ ፱ኛ የጾመ ሐዋርያት ፳፱ ፲ኛ| የጾመ ድኅነት ፩ ዕለት ይገኛል ከ፴ የተረፈው ተውሳክ ይባላል ተጨማሪ ማለት ነው ።

## ፬ኛ. ክፍል ።

በ፩ኛው መጽሐፍ ከገጽ ፰ት ላይ ወንጌላውያን በዓመት ጳጉሜን በዕለት አንድ ናቸው ብለን ነበር ነገር ግን የ፪ተኛዩቱ ጳጉሜንም ወንጌላውያኑም በዕለት ነው የሚቈጠረው ምክንያቱም በዓመት የሚገኙ ዕለታት ፫፻ ፷፭ ናቸው ፫፻፷፬ቱን በ፯ በ፯ት ገድፎ አምስተኛዩቱ ጳጉሜን ፩ ቀን ተርፍ አለች ስሟም ዕለተ ምርያ ይሏታል ወንጌላውያን በዓመት ተብሎ መቈጠሩ ከዓመት ገብታ ስለ ተቈጠረች ነው እንጂ የምትቈጠረውስ ዕለቷ ብቻ ናትና እናስተውል እንዲሁም በ፩ኛው መጽሐፍ ከገጽ ፲፩ ላይ ስለ ኬክሮስ አቈጣጠር የቀረውን ከዚህ እንገልጻለን ኬክሮስ ማለት በዛሬው የሥልጣኔ አቆጣጠር ስንተረጒመው ፩ዱ ኬክሮስ ፲፪ ደቂቃ ማለት ነው ፫ቱ ኬክሮስ ፫ ደቂቃ

www.ethiopianorthodox.org

ይሆናል ። አንድ ሰዓት ማለት ነው ከ፩ዱ ወንጌላዊ የተ ገኘ ፲፭ት ኬክሮስ ሲሆን ። ከ፫፻፷፭ ቀኖች ውስጥ ትርፍ ፫ ሰዓት ይገኛል ማለት ነው ይህ ቍጥር ከ፩ዱ ዓመት ፫ ሰዓት ከ፬ቱ ዓመት ፲፪ ሰዓት ስለሚገኝ አባቶቻችን ፮ኛዩቱ ጳጉሜን በ፬ት ዓመት የምትገኝበትን ሂሳብ ጠን ቅቀው መዝግበው አቆይተውናል ይኸም ቍጥር በዛሬው የሥልጣኔ አቈጣጠር ስንተረጕመው ፍራክሽን የሚባ ለው ይህ ነው አባቶቻችንም ጠቃቅን ብለውታል ስለ ዚህ ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የሠለጠኑ ናቸውና የዛሬ ልጆችም ሥልጣኔውን በማስፋፋት ላይ ስለምትገኙ አባቶቻችሁን መንቀፍ የለባችሁም ።

## ፯ኛ ክፍል ።

ዓውደ ጥንተ ዮን ከረቡዕ እስከ ማክሰኞ ነው፤ ዓውድ ማለትም መመላለሻ ማለት ነው ። ጥንተ ዮን ከምን ይገኛል ቢሉ በዓመት የሚገኙ ቀኖች ፫፻፷፭ ቀኖችና እን ዲሁም ፲፭ት ኬክሮስ ይገኛል ። ስለ ኬክሮሱ በ፯ኛው ክፍል ተመልክት ዕለተ ምርያ ፭ተኛዩቱን ጳጉሜን ለማ ግኘት ፫፻፷፭ቱን ቀን በ፯ት በ፯ት ቢገድፉ ዕለተ ምርያ የምትባል ፭ኛዩቱ ጳጉሜን ፩ዷት ቀን ትተርፋለች።

ዕለተ ምርያ የተባለችው ፩ዷት ቀን እስከ ዛሬ ድረስ (ማለት እስከ ፲፱፻፶፯ ዓ. ም.) ፯ሺህ፬፻፶፯ ቀን ሁናለች ዕለተ ምርያ ከ፬ት ከፍለን ዕለተ ሠግር ፮ተኛዩቱን ጳጉሜን ጨምረን በ፯ት በ፯ት እየገደፍን ከሱባኤ የተረፈውን ፩ዱን አትተን ሱባኤ ማለት ፯ት ማለት ነው ። አትተን ማለ



ትም ትተን ማለት ነው) ከ፯ት የተረፈው ጥንተ ዮን ይሆ ናልና ጥንተ ዮን ከፀሐይ ዓውደ ዓመት ተገኘ ይሏል ።

፲፭ ኬክሮስ በምን ይታወቃል ቢሉ መጋቢት ፳፭ ቀን መዓልትና ሌሊት ይተካከላሉ ። ከዚህም ቀጥሎ እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን መዓልት ከሌሊት ፩ድ ፩ድ ከንትሮስ ይወስዳል ከንትሮስ ብሂል ፩ዱ ክፍል እምዘ ይከፍልዎ ለ፩ዱ ሰዓት ኀበ ፴ እንዳለ ። ፴ው ከንትሮስ ፭ት ኬክሮስ ይሆናል ። ፭ት ኬክሮስም ፩ድ ሰዓት ነው ብለናል ። በዚሁ ቍጥር ፺ ከንትሮስ ፫ት ሰዓት ይሆናል ። ፫ት ሰዓትም ፲፭ ኬክሮስ ይሆናል ። ፩ድ ከንትሮስ በዘመናዊው ሥልጣኔ አቈጣጠር ፪ት ደቂቃ ማለት ነው ። ስለዚህ ጥንታዊው አቈጣጠር ወይም አነጋገር ። ወደ ሐዲሱ ሥልጣኔ ሲተረጐም የቀድሞ አባቶቻችን በጣም አዋቂዎች ነበሩ ለማለት እንችላለን ።

ሌሊቱንም ቢሹ ከሰኔ ፳፭ ቀን እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ፩ድ ፩ድ ከንትሮስ ከመዓልት ወደ ሌሊት ይመለሳል በመስከረም ፳፭ ቀን ዕሪና ይሆናል ። (መዓልቱና ሌሊቱ ልክ ይሆናል ማለት ነው) ከመስከረም ፳፭ እስከ ታኅ ሣሥ ፳፭ ቀን ድረስ ሌሊት ከመዓልት ፩ድ ፩ድ ከንትሮስ ይወስዳል ። ከታኅሣሥ ፳፭ ቀን እስከ መጋቢት ፳፭ ቀን ፩ድ ፩ድ ከንትሮስ ከሌሊት ወደ መዓልት ይመለሳል ሲሉ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን በደንብ አስተምረዋል ።

ይህ የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሊቅነትና ተመራማ ሪነት ምን ያህል ከፍተኛነት እንደነበረው እስኪ ልብ አድርገን እንመርምረው መዓልት ከሌሊት በቀን ፪ት

www.ethiopianorthodox.org

ደቂቃ አብልጦ መውሰዱን ተመልሶም ወደሌሊት መመ ለሱን ሌሊትም በተራው ከመዓልት በቀን ፪ት ደቂቃ አብ ልጦ መውሰዱን ። ተመልሶም ፪ት ፪ት ደቂቃ ወደ መዓ ልት መመለሱን ይህን ሁሉ የዓየርን ጠባይ መርምሮ ማወቅ ከማን ተገኘ ከአባቶቻችን ነው ።

በዛሬው ዘመን የሳይንስ ሊቃውንትም በማሻሻል እውቀታቸውን እያሳደጉ ከሥራ ላይ እንዲውል ሁሉም እንዲያውቀው በማድረጋቸው ይመሰገኑበታል እንጂ መሠ ረቱስ ከቀደሙ አባቶች የተገኘ ነው ።

ስለዚህ በዓመት በዓመት የሚገኙ ፭ቱ ቀኖችና (ማለት ጳጉሜን) በ፬ኛው ዓመት የምትገኘው ፮ተኛዪቱ ጳጉሜን ከዓውደ ፀሐይ የተገኙ ናቸው ይሏል ።

ይህም ሁኔታ በሦስተኛው መጽሐፍ ተብራርቶ ይጻፋል ።

## ፰ኛ ክ ፍ ል ።

ጥያቄ በዓላትንና አጽዋማትን መሠረታቸውን ለቀው በማ ሻሻል ከተወሰኑላቸው ቀን እንዲውሉ ያደረገ ማን ነው ?

መልስ ቅዱስ ድሜጥሮስና በጊዜው የነበሩ ሊቃውንት ተስማምተው ነው ።

ጥ፡ አሁን ባለንበት ዘመን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ምን ማድረግ ይገባቸዋል ?

መ፡ የጊዜውን ሁኔታ እያዩ በማሻሻል ሃይማኖትን መሠ ረት አድርገው በሕፃናቱ አእምሮ የሚቀረጹ ጥናቶች ማስተማርና ማስጠናት አለባቸው



ጥ፡ አበቅቴ ማለት ምን ማለት ነው

መ፡ ተረፈ ዕለት ቍጥር ማለት ነው

ጥ፡ መጥቅዕ ማለት ምን ማለት ነው አስረዳኝ

መ፡ ነጋሪት ማለት ነው በቁሙም መጥቅዕ ይባላል ትር ጓሜውም ሰብሳቢ ማለት ነው

ጥ፡ የዕለታት ተውሳክ በምን ይጀመራል አስረዳኝ

መ፡ በቀዳሜ ይጀመራል

ጥ፡ የቀዳሜ ተውሳክ ስንት ነው አስረዳኝ

መ፡ የቀዳሜ ተውሳክ ፰ት ነው

ጥ፡ የዕለታት ተውሳክ በምን ይጨርሳል አስረዳኝ

መ፡ በዓርብ ይጨርሳል

ጥ፡ የዓርብ ተውሳክ ስንት ነው አስረዳኝ

መ፡ የዓርብ ተውሳክ ፪ት ነው

ጥ፡ ተውሳክ ማለት ምን ማለት ነው

መ፡ ተጨማሪ ማለት ነው

ጥ፡ ከቀዳሜ እስከ ዓርብ ያሉ ዕለታት ተውሳካቸውን በየአንድ አንዳቸው ለይተህ አስረዳኝ

መ፡ የቀዳሜ ፰ት የእሁድ ፯ት የሰኞ ፮ት የማክሰኞ ፭ት የረቡዕ ፬ት የሐሙስ ፫ት የዓርብ ፪ት ነው

ጥ፡ ተውሳከ ዕለት ከምን ይገኛል አስረዳኝ

መ፡ በዓለ መጥቅዕ የዋለበትን ትተን ነነዌ እስከ ዋለበት ቀን ቈጥረን በ፯ት በ፯ት ስንገድፈው በዘመኑ የተ ገኘ ተውሳከ ዕለት ትርፍ ሆኖ ይገኛል

ጥ፡ ነነዌ ከዋለበት ሳኒታ አንሥተህ እስከ ነነዌ የዋለ

www.ethiopianorthodox.org

በትን ቀን ቈጥረህ በጠቅላላው የኀ፡ቱን ቀኖች ተውሳክ እንደምን እንደሚገኝ አውጥተህ አስረዳኝ

መ፡ መጥቅዕ ቅዳሜ ቢውል እሁድን ይዘን እስከ ነነዌ ብንቈጥር ፻፳፰ እሁድ ቢውል ፻፳፯ት ሰኞ ቢውል ፻፳፮ ማክሰኞ ቢውል ፻፳፭ት ረቡዕ ቢውል ፻፳፬ት ሐሙስ ቢውል ፻፳፫ት ዓርብ ቢውል ፻፳፪ት ይሆናል በየአንድ አንዱ ፻፳ውን በ፴ በ፴ ቢገድፉት ተውሳከ ዕለቱን ትርፍ ሁኖ እናገኘዋለን ።

ጥ፡ የዓቢይ ጾም ተውሳክ ስንት ነው አስረዳኝ

መ፡ የዓቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ነው ።

ጥ፡ የደብረ ዘይት ፥ የሆሣዕና ፥ የስቅለት ፥ የትንሣኤ ፥ የርክበ ካህናት ፥ የዕርገት ፥ የጰራቅሊጦስ ፥ የጾመ ሐዋርያት ፥ የምህላ ድኅነት ተውሳካቸው ስንት ስንት እንደሆነ ለይተህ አስረዳኝ ?

መ፡ የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ ፤ የሆሣዕና ፪ት ፤ የስቅለት ፯ት ፤ የትንሣኤ ፱ኝ ፤ የረክበ ካህናት ፫ት ፤ የዕርገት ፲፰ት ፤ የጰራቅሊጦስ ፳፰ት ፤ የጾመ ሐዋርያት ፳፱ ፤ የምህላ ድኅነት ፩ድ ነው ።

ጥ፡ ይህ የአጽዋማት ተውሳክ ከምን ይገኛል አስረዳኝ?

መ፡ ዓቢይ ጾም ብቻ ነነዌ የዋለበት ሰኞን ትተን ከማክሰኞ እስከ ዓቢይ ጾም ስንቈጥር ፲፬ ቀን ይሆናል ። የዓቢይ ጾም ተውሳክ ይህ ነው ። እስከ ደብረ ዘይት ፵፩ እስከ ሆሣዕና ፷፪ት እስከ ስቅለት ፷፯ት እስከ ትንሣኤ ፷፱ እስከ ረክበ ካህናት ፺፫ት እስከ ዕርገት ፻፰ት እስከ ጰራቅሊጦስ ፻፲፰ት እስከ ጾመ ሐዋርያት ፻፲፱ እስከ ጾመ ድኅነት ፻፳፩ ዕለት ይገኛል ። በየ፩ድ ፩ዱ በ፴ በ፴ ስንገድፈው ተውሳኩን ትርፍ ሁኖ እናገኘዋለንና ከዚህ የተገኘ ነው ።



ጥ፡ አጽዋማትና በዓላት የተወሰነላቸውን ቀን ለማግኘት በየ፩ድ ፩ዳቸው የሚመላለሱበት ቀን ስንት ነው አስረዳኝ ?

መ፡ መመላለሻቸው ፴፭ት ፴፭ት ቀን አላቸው ።

ትርፍ ጥያቄ በጠቅላላው በዓመት ውስጥ የሚገኙ አጽዋማት ፴፭ት ቀን መመላለሻ አላቸውን ?

መ፡ ከነነዌ ጀምሮ እስከ ምህላ ድኅነት ያሉ በዓላት ብቻ ናቸው ።

ጥ፡ የነነዌና የዓቢይ ጾም መመላለሻቸው የሚወጡበትንና የሚወርዱበትን ፴፭ ቀን ለይተህ አስረዳኝ

መ፡ ነነዌ ቢወርድ ከጥር ፲፯ት በታች አይወርድም ቢወጣም ከየካቲት ፳፩ ቀን በላይ አይወጣም ። መመላለሻው ከጥር ፲፯ት ቀን እስከ የካቲት ፳፩ ቀን ፴፭ት ይሆናል ። ዓቢይ ጾም ከየካቲት ፩ድ ቀን በታች አይወርድም ፥ ከመጋቢት ፭ት ቀን በላይ አይወጣም፤ መመላለሻው ከየካቲት ፴ ቀን ከመጋቢት ፭ ቀን ፴፭ ይሆናል መመላለሻው ይህ ነው ።

አስተማሪው በቃል እስከ ምህላ ድኅነት ያለውን መመላለሻ መጽሐፉን እያየ ያስረዳ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፱ኛ ክፍል ።

ጥ፡ ጥንታውያን አባቶቻችን የሂሳብ ትምህርት አላቸውን ወይስ የላቸውም አስረዳኝ

መ፡ በደንብ አላቸው ።

ጥ፡ ማብዛት መቀነስ መደመር ማካፈል እንደዛሬው ትምህርት ያስተማሩበት መጽሐፍ ይገኛልን

መ፡ አዎን በየቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ይገኛል ።

ጥ፡ ዓለም ከተፈጠረ እስከዛሬ ድረስ (ማለት እስከ ፲፱ ፻፶፯ ዓ. ም.) ስንት ዘመን ሁኗል አስረዳኝ ።

መ፡ ፯ት ሽህ ፬፻፶፯ት ዘመን ነው ።

ጥ፡ ለ፬ቱ ወንጌላውያን ሲከፈል ስንት ስንት ይደርሳቸዋል ?

መ፡ ሽህ፰፻፷፬ ሽህ፰፻፷፬ት ዓመት ይደርሳቸዋል ።

ጥ፡ ለ፬ቱም ክፍል ልክ የደረሰበት ምክንያት ምንድር ነው አስረዳኝ ?

መ፡ ዘመኑ ዘመነ ዮሐንስ ሲሆን አይተርፍም ልክ ይደርሳቸዋል ።

ጥ፡ የ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ወንጌላዊ ማን ነው ?

መ፡ ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው ።

ጥ፡ ፲፰፻፷፬ት ዘመን በጥንታውያኑ አባቶቻችን አከፋፈል በጽሑፍ ለ፯ት ክፍለህ አሳየኝ ?

መ፡ ጥንታውያን አባቶቻችን ሲያካፍሉ የማካፈሉን



ጥናት በቃል ነበር የሚያስጠኑት ሆኖም በቃል እን ዳጠናሁት ከዚህ በታች አሳያለሁ ።

፪፻፷፮
፲፰፻፷፬ ÷ ፯ት ጊዜ
፲፬፻
፬፻፷
፬፻፳
፵፬
፵፪
፪ ሁለት ትርፍ ነው የተባለው ይህ ነው ።

ጥ፡ በዛሬው ቁጥር ሠርተህ አሳየኝ

መልስ
266
1864 ÷ 7
14
46
42
44
42
2

ይህ ስለ ተሻሻለ በጣም ቀለል ይላል ፤ ሥራውም ይህ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥ፡ ፩ድ ቀን ስንት ኬክሮስ ነው አስረዳኝ ።
መ፡ ፷ ኬክሮስ ነው ።
ጥ፡ አንድ ኬክሮስ በዛሬው አቈጣጠር ስንት ደቂቃ ነው ።
መ፡ ፳፬ ደቂቃ ነው ።

ጥ፡ አንድ ከንትሮስ ስንት ደቂቃ ነው አስረዳኝ ።
መ፡ ፬ት ደቂቃ ነው ።

ጥ፡ ፴ ከንትሮስ ስንት ኬክሮስ ይሆናል ።
መ፡ ፭ት ኬክሮስ ይሆናል ፥

ጥ፡ አባቶቻችን ትናንሹን ቊጥር ምን ይሉት ነበር ።
መ፡ ጠቃቅን ይሉት ነበር ።

ጥ፡ በዛሬው ሥልጣን አቈጣጠር ጠቃቅኑ ምን ይባላል አስረዳኝ ።
መ፡ ፍራክሽን ይባላል ።

መልሱ መልካም ነው ፪ኛው መጽሐፍ ተፈጸመ ሦስተኛው መጽሐፍ ይቀጥላል ።

አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው ። አሜን ።

መ| ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ፤

---



# ማ ሳ ሰ ቢ ያ ።

በ፩ኛው መጽሐፍ በ፪ኛው ክፍል ስለ፮ተኛዩቱ ጳጉሜን አቈጣጠር ፲፭ ኬክሮስ ብቻ ይዞ ዓመታትን መቊጠር በማቴዎስ ይጀመራል ካለ በኋላ የማቴዎስ ፲፭፡ የማርቆስ ፲፭ የሉቃስ ፲፭ ድምሩ ፷ ኬክሮስ ይሆናል በ፬ኛው ዓመት በዘመነ ሉቃስ ስድስተኛዩቱ ጳጉሜን ትገኛለች የሚባለውን ንባብ ፩ኛ ኬክሮስ ማለት ምን እንደሆነ ፪ኛ ይህ የተባለው ፲፭ ኬክሮስ ከየትኛው ወር እንደሚገኝ ስላልገባን ተብራርቶ ይገለጽልን፤ ብለው ብዙዎች ስለ ጠየቁኝ ከዚህ ቀጥየ የ፮ተኛዩቱን ጳጉሜን አቈጣጠር በተለይ አስረዳለሁ።

ይኸውም በአሁኑ ዘመን ማለት ከ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. ጀምረን እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ ም ድረስ እንዴት ሆኖ እንደ ሚቈጠር እገልጻለሁ ።

፩ኛ መስከረም ፩ ቀን የሚውለው ፲፪ ሰዓትና ፬ት ካልኢት ከ፴ ሣልሲት ነው በዘመናዊው ቊጥር ላስረዳ እፈቅዳለሁ፤ ፩ድ ኬክሮስ ፳፬ ደቂቃ ነው ፭ ኬክሮስ ፪ ሰዓት ይሆናል ፪ኛ| ፩ድ ክልኢት ፮ት ሰከንድ ማለት ነው ፫ኛ ፩ ሣልሲት ፫ት የሰከንድ ሰከንድ ነውና አስተውሉ በዚህ ቊጥር እስከ ወር ፴ ቀንና ፩ ኬክሮስ ከ፲፭ ካልኢት ይሆናል ።

፪ኛ| በጥቅምት ወር እንደዚሁ ፴ ቀንና ፩ ኬክሮስ ከ፲፭ ካልኢት

www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ| በኅዳር ወር እንደዚሁ ፴ ቀንና ፩ ኬክሮስ ከ፲፰ ካልኢት

፬ኛ| በታኅሣሥ ወር እንደዚሁ ፴ ቀንና ፩ ኬክሮስ ከ፲፰ ካልኢት ይሆናል ፬ት ጊዜ ፲፰ት ፸ ካልኢት ይሆናል ፸ ካልኢትም ፩ድ ኬክሮስ ነው በታኅሣሥ ፴ ቀን ፬ ወር ከ፰ ኬክሮስ ይሆናል (፬ ወር ከ፩ድ ሰዓት ማለት ነው ።

፭ኛ| በዚሁ አቈጣጠር ከጥር ፩ድ ቀን እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፬ት ወር ከ፰ት ኬክሮስ ይሆናል ።

፮ኛ| ከግንቦት ፩ ቀን እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ፬ት ወር ካ፰ት ኬክሮስ ነውና አስተውሉ በ፬ት ወር ፩ድ ሰዓት በ፬ት ወር ፩ ሰዓት ሲሆን በ፲፪ት ወር ፫ ሰዓት ተሠርቶበት አለፈ ማለት ነው በ፲፱፻፶፮ ዓ ም በዘመነ ዮሐንስ ነሐሴ ፴ ቀን ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል (ማስጠንቀቂያ) ፰ት ቀን ጳጉሜን ከካልኢት የተገኘ ስለሆነ ኬክሮስና ካልኢት የለውም ከ፲፪ቱ ወር ብቻ ነው የሚቈጠረውና አስተውሉ ። በዘመነ ማቴዎስ ፶፯ ዓ ም እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ። በዘመነ ማርቆስ ፶፰ ዓ ም እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል። በዘመነ ሉቃስ ፶፱ ዓ ም እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ማለት።በ፲፱፻፶፱ ዓ ም በዘመነ ሉቃስ የስድስተኛዩቱ ጳጉሜን ቍጥር በነሐሴ ፴ ቀን ከላይ እንደተዘረዘረው ተስብስቦ ሙሉ ፲፪ ሰዓት ይሆናል ።



ነገር ግን የነሐሴ ወር በ፬ኛው ዓመት ፴፩ ቀን መሆን ሲገባው የጥርቅም ቍጥር ስለሆነ ከ፮ቱ ቀን ጳጉሜን በኋላ ፯ኛ ቀን እንድትሆን ተደርጓል ከዚህ ውስጥ ያለ ማሻሻል ማስተዋል በቂ ነው ።

ከዚህ የቀረው በ፫ኛው መጽሐፍ ከ፫ኛ ክፍልና ከ፯ኛው ክፍል ተመልከት ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ተዘጋጅ ተው የታተሙት መጻሕፍት ።

፩ኛ. የደር ሡልጣንና ኀልጎታ የኢትዮጵያ ገዳም አስረጅ በኢየሩሳሌም በ፲፱፻፶ ዓ. ም.

፪ኛ. ርትዕት ይእቲ ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ በ፲፱፻፶፪ ዓ. ም.

፫ኛ. ስለ ደር ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

፬ኛ. ፩ኛ. መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ታትሟል ።

፭ኛ. ፪ኛ. መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ። በ፲፱፻፶፱ ዓ. ም. መስከረም ፯ ቀን ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ረ ሚ ያ ፤

| ግድፈት ፥ | እርም ፤ | ገጽ | ክፍል |
|---|---|---|---|
| ሠርቀ ዕለትን ማግኘት ፤ | ሠርቀ ዕለትን ለማግኘት ፣ | ፲ | ፫ |
| ጳጒሜን ፩ ቀን ተርፍ አለች ፤ | ፩ ቀን ትተርፋለች ፤ | ፲፯ | ፯ |
| ነነዌ ከዋለበት ሳኒታ እንሥተህ እስከ ነነዌ ፤ | መጥቅዕ ከዋለበት ሳኒታ እንሥተህ እስከ ነነዌ ፤ | ፳፩ | ፰ |

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org